# ምድብ አንድ (የሙዓለ ሕፃናት ተማሪዎች)

## 26 ኛ ሳምንት

## ልጆች ክርስቶስን ተቀበሉት

**ዓላማ**

- ክርስቶስ በክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱንና እንዴት እንደተቀበሉት መማር።

**ምንባብ**

- ማቴ. 21÷1-16

**መግቢያ**

- ከዚህ በፊት ክርስቶስ ስለተወለደበት ቦታና ስለፈጸማቸው ተዓምራት የተማራችሁትን ታስታውሳላችሁ?....እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፤እመቤታችንም እናቱ ናት።ዘላለማዊ ንጉሥም ነው።
- ዛሬ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ ልጆች እየዘመሩ የተቀበሉበትን ታሪክ እንማራለን።

**ትምህርቱ**

- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ብዙ ተዓምራት ፈጽሞል።
- አዎን እርሱ ሽባውን እንዲራመድ፣እውራኑ እንዲያዩ፣የማይሰሙት እንዲሰሙ አድርጓል።
- አንድ ቀን÷አይሁድ በኢየሩሳሌም በዓል የሚያከብሩበት ቀን ነበርና ብዙ ሕዝብ ለበዐሉ ተሰባስበው ነበር፤ክርስቶስም በአህያ ተጭኖ ወደ ኢየሩሳም ገባ።
- ብዙ ተዓምራት ሲያደርግ ይሰሙ ስለነበር የተሰበሰቡት ሕዝብ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም መምጣቱን ሲሠሙ ሊቀበሉት ፣ሊያዩትም ወጡ።
- ጌታችን በአህያይቱ ላይ ተጭኖ ሲገባም፣የዘንባባ ዝንጠፊ፣የዛፍ ቅጠል ጫፍ፣ ልብሳቸውንም እያነጠፉ በክብር ተቀበሉት።
- በዚህ ዕለት ልጆች፣በእናታቸው እቅፍ የተያዙ ሕጻናትም ሊያዩት መጥተዋል። እንዲህ ሲሉም ዘምረዋል፡ ***« በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፤ ሆሣዕና በአርያም።»***

**ሙከራ**

1.የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ማናት?

---

2.ጌታችን ምን ዓይነት ተዓምራትን ፈጸመ?

---

3.ሕዝቡ በእየሩሳሌም የተሰበሠበው ለምን ነበር?

---

4.ጌታችን ወደ ኢየሩሳሌም መምጣቱን ሲሰሙ ምን አደረጉ?

---

**መዝሙር**

ሆሣዕና በአርያም

እያሉ ዘመሩ ሕፃናት በኢየሩሳሌም

እያሉ ዘመሩ ሕፃናት በኢየሩሳሌም

# The Triumphal Entry



**ይቆየን፡፡**